የሰ/መ/ቁ. 52459

ሐምሌ 16 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ ወ/ሮ ሙሉ ታደሰ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አለሙ መራ ኮንስትራክሽንና ጠቅላላ ብረታ ብረት ስራ ድርጅት

- ባለቤት ወ/ሮ አልማዝ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት በተጠሪ ድርጅት ሲሰሩ ከዚህ አለም በሞት ስለተለዩ የስንብት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ስለተደረገባቸው የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካቾች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት በተጠሪ ድርጅት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዘበኛነት ተቀጥረው ሲሰሩ የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው የሚገባቸው የአገልግሎት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ የተጠሪ ድርጅት ባለቤት ቀርበው በሰጡት መልስ የጋራዥ ስራውን መስራት ባለመቻላቸው ለሌላ ሰው በኮንትራት የሰጡ መሆኑንና ሟች ከሳቸው ጋር ያለውን ስራ ውል ከሰኔ 1 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ ተቋርጦ ስራውን በኮንትራት ከያዘው ሰው ጋር ተዋውለው ይሰሩ ስለነበር ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአንደኛ አመልካች ባለቤትና የቀሪዎቹ አመልካቾች አባት የስራ ውል የተቋረጠው በሞት ምክንያት በመሆኑና በዚህ ሁኔታ የስራ ውል ሲቋረጥ የስንብት ክፍያ እንዲከፈል የሚያስገድድ ህግ ስለሌለና የአመት እረፍትም ቢሆን በሞት ምክንያት የስራ ውሉ ለተቋረጠ ሰራተኛ ስለማይሰጥ ጥያቄውን ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በቅሬታቸው የስር ፍ/ቤት የሟች አገልግሎት ክፍያም ሆነ የአመት እረፍት ለሚስታቸውና ለልጆቻቸው አይከፈልም መባሉ ስህተት በመሆኑ እንዲታረምላቸው አመልክተዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሟች የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ለአመልካቾች ሊከፍል አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ የሟች ስራ ውል የተቋረጠው ከሞታቸው በፊት በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን ከተያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካቾች የጠየቁት የሟቹ አገልግሎት ክፍያና አመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄን በተመለከተ ለሰበር ችሎት ያስቀርበዋል ያልተባለ ከመሆኑም ባላይ ይህን ነጥብ አስመልክቶ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 45264 ከሰጠው ትርጉም ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ይህንኑ ቅሬታ የምንመለከተው አይሆንም፡፡ ሁለተኛው የክፍያ ጥያቄ የአመት እረፍትን የሚመለከት ነው፡፡ በአ/ቁ 377/1996 አንቀፅ 77(5) በአዋጁ መሰረት የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ያልወሰደው የአመት ፈቃድ ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ እንደሚሰጠው ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ የሚሰጠው በአዋጁ ከተደነገጉት የስራ ማቋረጫ ምክንያቶች በተወሰኑት ምክንያቶች ብቻ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ነው የሚል ገደብ አላስቀመጠም፡፡ በመሆኑም በማንኛውም በአዋጁ

በተመለከቱ ድንጋጌዎች የስራ ውሉ ከተቋረጠ የሰራተኛው የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዋጁ መሰረት የስራ ውል ከሚቋረጥባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የሰራተኛው መሞት እንደሆነ ከአንቀፅ 24(2) የምንገነዘበው ነው፡፡ በመሆኑም የሰራተኛው የስራ ውል በሰራተኛው ሞት ምክንያት ከተቋረጠ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ለወራሾቹ ሊከፈል የማይገባበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት የስራ ውሉ በሞት ምክንያት ሲቋረጥ የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል አይገባም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን ተጠሪ ከስር ጀምሮ በተጠሪና በአንደኛ አመልካች ባለቤት እና በቀሪዎቹ አመልካቾች አባት መሃከል የነበረው የስራ ውል ሰኔ 1994 ዓ.ም የተቋረጠና ሟች ጋራዡን በኮንትራት ከያዙት ሰው ጋር ባደረጉት የስራ ውል የሚሰሩ ስለመሆኑ የሚከራከሩ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ይህን የአመልካች ክርክር ሳይመለከት ማለፉን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን የሟቹ አመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል የሚገባ ቢሆንም ተጠሪ ክፍያውን የመፈፀም ሃላፊነት ያለባቸው መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39535 ህዳር 7 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 86994 ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾች የሟች የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡ ነገር ግን የስራ ውሉ በሞት ምክንያት በመቋረጡ የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈል አይገባም የሚለው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የስር ፍ/ቤት በሟችና በተጠሪ መሃከል የስራ ውል መኖር አለመኖሩን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ማስረጃ አኳያ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ